የሰበር መ/ቁ. 24295

መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ደስታ ገብሩ

ሒሩት መለሠ

መድሕን ኪሮስ

**አመልካች ፡-** ወ/ሮ ጽጌ ድረሴ

**ተጠሪ ፡-** ወ/ሮ መሰለች ረዳ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ ስትሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው ከሟች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት ያለችውን ንብረት እንድታስረክባት ነው፡፡ አመልካችም ለቀረበባት ክስ መልስ ሰጥታለች፡፡ ፍ/ቤቱም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ ክስ የቀረበባቸውን ንብረቶች /መኖሪያ ቤት እና ልዩ ልዩ የቤት ቁሳቁሶች/ ለከሳሽ ታስረክብ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተመሳሳይ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ሚያዝያ 9 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ከሟች ባለቤትዋ ጋር አፈራሁት የምትለውን ንብረት በሙሉ መጠየቅ ስለመቻል አለመቻልዋ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡



በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ የንብረት ይገባኛል ጥያቄ ያነሳችው የሟች ሚስት መሆንዋንና በዚህ መሠረትም ንብረቱ በጋራ ያፈሩትው እንደሆነ በመግለጽ ነው፡፡ አመልካችም ተጠሪ የሟች ሚስት አይደለችም ወይም በተባለው ንብረት ላይ የጋራ መብት የላትም የሚል ክርክር አላነሳችም፡፡ አመልካች ያነሳችው አንድ መቃወሚያ ሲሆን፣ ይህም የቤቱ ግምት ተጋኖአል የሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መቃወሚያውን በመቀበል ቤቱን በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል እንዲገመት አድርጐአል፡፡ በዚህ መሠረትም ቤቱና በዝርዝር የተገለጹት የቤት ዕቃዎች እንዳሉ ለተጠሪ እንዲሰጡ ወስኗል፡፡

እንደምንመለከተው ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ቤት እና የቤት ዕቃዎች የባልና ሚስት የጋራ ሃብቶች ናቸው፡፡ በንብረቶቹ ላይ ባልና ሚስቱ ያላቸው መብት እኩል አይደለም የሚል ክርክር አልተነሳም፡፡ በባልና ሚስቱ መካከል የነበረው ጋብቻ በባልየው ሞት ምክንያት ፈርሶአል፡፡ ጋብቻ ሲፈርስ በንብረት ክፍፍል ላይ የራሱ የሆነ ውጤት እንደሚኖረው በቤተሰብ ሕጉ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች በግልጽ ተለይተው የታወቁ ናቸው፡፡ አንደኛው ተጋቢ ከሌላኛው ተጋቢ ወገን የበለጠ ወይም ያነሰ መብት አለው የሚል ክርክርም አልተነሳም፡፡ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ እኩል የሆነ /የጋራ/ መብት እንዳላት ከመግለጽ አልፋ ከድርሻዋ በላይ የምትወስድበት ምክንያት እንዳላት አላስረዳችም፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁ. 213/92 አንቀጽ 90 እንደተደነገገው የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተጠሪ መጠየቅ ያለባት ወይም ልታገኝ የሚገባት የንብረቶቹን ግማሽ ብቻ ነው፡፡ ግማሹ የሟች ባለቤትዋ ድርሻ በመሆኑ ይህንኑም ጠቅልላ የምትወስድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

የስር ፍ/ቤቶችም ይህን በሕግ የተመለከተውን የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ክፍፍል ሥርዓት ባለመከተል ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00676 መጋቢት 30 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38807 መጋቢት 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ መውሰድ ያለባት ድርሻዋ ማለትም የቤቱ እና የቤት እቃዎቹ ግማሽ ነው ብለናል፡፡ በዚህ መሠረት ክፍፍሉ እንዲፈፀም ለስር ፍ/ቤቶች ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ዙ/ዘ



የሰ/መ/ቁ. 24625

ጥቅምት 28 ቀን 2000 ዓ.ም.

ዳኞች፡- አብዱልቃድር መሐመድ
ሐጎስ ወልዱ
ተገኔ ጌታነህ
ተሻገር ገ/ሥላሴ
ብርሃኑ አመነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራሕማ ዓሊ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው የንብረት ይገባኛል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተችው ተከሣሽ የሟች ባለቤቴ ማሩ ሱሌይማን ንብረት የሆነ ቤት ይዛ ስለምትገኝ የእኔንና ከሟች የወለድኩትን ልጄን ድርሻ ታካፍለን በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የሁለቱንም ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ፣ ከሣሽና ተከሣሽ የሟች ሚስቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም የቤቱን ግማሽ ሁለቱ ይካፈሉ፡፡ ግማሹን ደግሞ ለልጁ ይሁን በማለት ሲወስን፣ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛ ፍ/ቤት ግን ቤቱ የተገዛው ሟች እና ተጠሪ ባፈሩት ገንዘብ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካች ከቤቱ ልትካፈል አይገባም ሲል ወስኖአል፡፡ የመጨረሻውን ይግባኝ የሰማው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠ/ፍ/ቤትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አከራካሪው ቤት አመልካችና ማሩ ሱሌይማን በጋብቻ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ የተገዛ ሆኖ ሳለ፣ አመልካችና